# እግዚአብሔር የለወጠው ሰው!
## ዘፍጥረት 25-32

**"እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ፥ ሰውነቴም ድና ቀረች።" (ዘፍጥረት 32፡30)**

**መግቢያ**

ያዕቆብ በዘመኑ ሁሉ በትግል የኖረ ሰው ነው። በመጀመርያ ከዔሳው ጋር ታገለ፣ ቀጥሎም ከላባ ጋር ታገለ በመጨረሻም ከእግዚአብሔር ጋር ታገለ። እስቲ እነዚህ ሃሳቦች ግልጽ እንዲሆኑልን እያንዳንዳቸውን እንመልከታቸው።

I. **በመጀመርያ ያዕቆብ ከዔሳው ጋር ታገለ።**

1. **ያዕቆብ ከዔሳው ጋር ያደረገው ትግል የተጀመረው ገና በእናታቸው ማህጸን ውስጥ እያሉ ነው።**
   ***መጽሀፍ ቅዱስ "ልጆቹም በማህጸኗ ውስጥ እርስ በርሳቸው ይጋፉ ጀመር፤ ..." (ዘፍ 25፡22)*** **በማለት ይናገራል።**

ዘማሪው ሲናገር **"ወንድሞች በሕብረት ቢቀመጡ እነሆ መልካም ነው፣ እነሆም ያማረ ነው።" (መዝሙር 133፡1)** ይላል። ነገር ግን የያቆብንና የዔሳውን ነገር ስንመለከት ከማህጸን ጀምሮ መጋፋት፣ መጣላት፣ መጋጨት፣ አለመቀባበል፣ ወዘተ እንመለከታለን። አንድ ማህጸን አልበቃቸው አለ፤ አንድ ቤት አልበቃቸው አለ። ለያዕቆብና ለዔሳው የመጀመርያው የጦርነት መድረክ የእናታቸው ማህጸን ነበር።

እናት ያውም ልጅ መውለድ የማትችል (መካን የነበረች ሚስት) ነገር ግን በእግዚአብሔር ቸርነት ሕጻናትን ስታረግዝ (ማሕጸንዋ ዘርን ሲሸከም) በደስታ ልትሞላና ሀሴት ልታደርግ ሲገባት፤ ርብቃ ግን በኀዘን ተሞላች። ከሃያ ዓመታት በላይ በተስፋና በትዕግስት ትጠብቀው የነበረው ደስታና ሀሴት በማሕጸንዋ ውስጥ በሚካሄደው የልጆች ጠብና ጥል ምክንያት ሳታጣጥመው መቅረቷ አሳዛኝ ሆነባት። ከዚህ የተነሳ ለቤተሰቡ በአጠቃላይ በተለይም ለይስሐቅና ለርብቃ ደስታ ራቃቸው።

እኛስ? ታሪካችንን ወደኋላ ዘወር ብለን ስንመለከተው እግዚአብሔር በአስደናቂ ሁኔታ በተስፋ ቃሉ እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ቤተ ክርስቲያን የጎበኘንና በረከቱን የለቀቀልን ሰዎች ነን። በአንድ ላይ እንድናመልከውና እንደ ቤተሰብ አብረን በቅዱሳን ሕብረት እንድንር ሁኔታን ሁሉ አመቻችቶልናል። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ቤት ሰፊ ሆኖ ሳለ በጠብና በግጭት ምክንያት ቤቱ አልበቃ ብሎን ይሆን? በክርስቶስ የተዋጁ ወንድሞችና እህቶች አብረው ሲኖሩ መልካም፣ ያማረ፣ አስደሳችና ሰማያዊ በረከትን የምንሰበስብበት ሊሆን ሲገባ ስምምነት ካለመኖሩ የተነሳ ደስታችን ተገፍፎና በሐዘን ድባብ ውስጥ ገብተን ይሆን? ቤተ ክርስቲያን ግራ ገብቷት ይሆን?

እናታቸው ርብቃ ይህ ሁኔታ በሕይወቷና በትዳርዋ ሲከሰት ***"ለምን እንዲህ ይሆንብኛል?"*** (25፡22) ብላ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ሄደች። ከመካንነት መውጣት የደስታ ምንጭ ነው፤ ለባልና ሚስት ሐሴት ያመጣል። ነገር ግን ጠብና ግጭት እንዲሁም የማያባራ ትግልና ፍልሚያ በልጆች መካከል በማጸን ውስጥ ሲከሰት ይህን ጥያቄ ይዛ ወደ እግዚአብሔር መቅረቧ ትክክል ነበር።

እግዚአብሔርም እንዲህ የሚል መልስ ሰጣት፡-

> ***"ወገኖች በማህጸንሽ ውስጥ አሉ፤
> ሁለትም ሕዝቦች ከውስጥሽ ተለያይተው ይወጣሉ፤
> አንደኛው ከሌላው ይበረታል፤
> ታላቁም ለታናሹ አገልጋይ ይሆናል አላት፡፡" (25፡23)***

ምንም እንኳ በወቅቱ በነበረው ባህል መሰረት ታናሽ ለታላቅ ሊገዛ ቢገባውም ከላይ ባነበብነው የእግዚአብሔር ንግግር እንደምንመለከተው እግዚአብሔር በመለኮታዊ ምርጫው ታናሹን ልጅ ያዕቆብን በጸጋው መምረጡ ግልጽ ነው፡፡

> ***"… ያዕቆብን ወደድሁት፤ ዔሳውን ግን ጠላሁት፤ …" (ሚል 1፡2)***

በእርግጥም ያዕቆብ ገና ከእናቱ ማህጸን ጀምሮ በእግዚአብሔር የተመረጠ ሰው ነበር፡፡ በጣም የሚገርመው ነገር ግን ያዕቆብ ገና ከማሕጸን ጀምሮ እግዚአብሔር እንደ ተስፋ ቃሉ በሕይወቱ የሚፈጽመውን በረከት ከመጠበቅ ይልቅ በራሱ ትግል መለኮታዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ሃሳብ በሕይወቱ እውን ለማድረግ መሞከሩ ነው፡፡

በዘመናችንስ እግዚአብሔር የተስፋ ቃል ሰጥቶኛል እያሉ ነገር ግን ወንድሞቻቸውንና እህቶቻቸውን እየረገጡና በብልጣ ብልጥነት የሚሄዱ ይኖሩ ይሆን? ለመሆኑ የእግዚአብሔርን ፕሮግራም በስጋ ትግል በሕይወታችን ማስፈጸም እንችላለን?

2. <u>የያዕቆብና የዔሳው ትግል ሲወለዱም ተስተውሏል፡፡</u>

በመጀመርያ ዔሳው ከእናቱ ማህጸን ከወጣ በኋላ ወዲያውኑ ያዕቆብ ተከትሎ ተወለደ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ክስተት እንዲህ በማለት አስቀምጦታል፡-

> ***"ከዚያም ወንድሙ (ያዕቆብ) ተወለደ፤ በእጁም የዔሳውን ተረከዝ ይዞ ወጣ፤
> ከዚህም የተነሳ ስሙ ያዕቆብ ተባለ፡፡" (ዘፍ 25፡26)***

<u>"ያዕቆብ"</u> ማለት <u>"ተረከዝ ይይዛል"</u> ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በምሳሌያዊ አነጋገር <u>ያታልላል"</u> ማለት ነው፡፡ በአጭሩ <u>"ያዕቆብ"</u> ማለት <u>"አታላይ"</u> ማለት ነው፡፡

እግዚአብሔር በዘላለማዊ እቅዱ በአስደናቂ ሁኔታ የጠራውና የመረጠው ሰው ለምን የአታላይነት ባህርይ ከማሕጸን ጀምሮ ተጠናወተው?

3. <u>የዔሳውና የያዕቆብ ትግል ካደጉም በኋላ ቀጥሏል፡፡</u>

አንድ ወቅት ዔሳው እጅግ ተርቦ ከዱር ከአደን ከመጣ በኋላ ያዕቆብ ወጥ ሲሰራ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ዔሳው ያዕቆብን በጣም ርቦኛልና ከዚህ ከምትሰራው ቀይ ወጥ (ምስር ወጥ) አብላኝ በማለት ጠየቀው (25፡29-30)፡፡

> ***ያዕቆብም ወጥ ሠራ ዔሳውም ደክሞ ከበረሃ ገባ ዔሳውም ያዕቆብን፦ ከዚህ ከቀዩ ወጥ አብላኝ፥ እኔ እጅግ ደክሜአለሁና አለው፡፡ (ዘፍጥረት 25፡29-30)***

**"ያዕቆብም በመጀመርያ ብኩርናህን ሽጥልኝ"** (25፡31) በማለት ቅድመ ሁኔታ አስቀመጠበት፡፡ **"ዔሳውም፣ እነሆ፤ በረሃብ ልሞት ደርሻለሁ፤ ታዲያ ብኩርናው ምን ያደርግልኛል!"** በማለት በመሐላ ብኩርናውን ለያዕቆብ ሸጠለት፡፡ የእግዚአብሔር ቃል **"ዔሳው እንዲህ አድርጎ ብኩርናውን አቃለላት፡፡"** (25፡34) ይላል፡፡ ያዕቆብ ደግሞ በእንዲህ ዓይነት መንገድና ሁኔታ ብኩርናን ከዔሳው ወሰደ፡፡

4. <u>**የዔሳውና የያዕቆብ ትግል አባታቸው ይስሐቅ ዔሳውን ለመባረክ/ለመመረቅ በተዘጋጀበት ወቅት ታይቷል፡፡**</u>

ከዚም በኋላ ይስሐቅ በሸመገለና ዓይኖቹ ደክመው ማየት በተሳናቸው ጊዜ ልጁን ዔሳውን ለመባረክ/ለመመረቅ በማሰብ ካደነው እንስሳ ምግብ ሰርቶ እንዲያቀርብለት ለዔሳው ሲነግረው እንመለከታለን፡፡

ይሁን እንጂ ያዕቆብ በእናቱ በርብቃ አስተባባሪነት አባቱን ይስሐቅን በማታለል የዔሳውን በረከት/ምርቃት ከአባቱ ከይስሐቅ ተቀበለ ፡፡ (ዘፍ 27)

ይህ በማታለል የተፈጸመ ድርጊት እንደሆነ በጣም ግልጽ ነው፡፡ ያዕቆብ እናቱ ለርብቃ እንዴት የዔሳውን ምርቃት ከይስሐቅ መውሰድ እንዳለበት ስልቱን አመቻችታ ስትነግረው፡- "**አባቴ ቢዳስሰኝ <u>እንዳታለልሁት</u> ያውቃል፤**" (27፡12) በማለት ተናግሯል፡፡ ይስሐቅም ለዔሳው "**ወንድምህ መጥቶ <u>አታልሎኝ</u> ምርቃትህን ወስዶብሃል አለው፡፡**" (27፡35)

> "**ዔሳውም፣ ይህ ሰው ያዕቆብ መባሉ ትክክል አይደለምን? እኔን <u>ሲያታልለኝ</u> ይህ ሁለተኛ ጊዜው ነው፤ በመጀመርያ ብኩርናየን ወሰደብኝ፤ አሁን ደግሞ ምርቃቴን ቀማኝ አለ፡፡**" (27፡36)

ምንም እንኳ ያዕቆብ ገና በማህጸን ሳለ በእግዚአብሔር የተመረጠና መለኮታዊ የተስፋ ቃል የተሰጠው ሰው ቢሆንም ይህንን በረከትና የተስፋ ቃል ለማግኘት በራሱ መንገድ፣ ብቃት፣ ሃይል፣ ጉልበት፣ ዘዴ፣ እውቀት፣ ወዘተ የሚሄድ ሰው ነበር፡፡ የሚፈልገውን ነገር ለማግኘት ሲል ከሌሎች ሰዎች ጋር በመታገል የሚያምን አታላይ ሰው ነበር፡፡

ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱ የአታላይነት ሕይወት ያዕቆብን ለሽሽትና ለስደት ሲዳርገው እንመለከታለን፡፡ ዔሳው በያዕቆብ ላይ ቂም ያዘ፤ በልቡም የአባቴ መሞቻው ቀን ተቃርቧል፣ ከልቅሶው በኋላ ወንድሜን ያዕቆብን እገድላለሁ ብሎ ጊዜ ይጠብቅ ነበር፡፡ (27፡41-46)

ከዚህ የተነሳ ያዕቆብ እናቱ ርብቃ ባማከረችው መሰረት ሕይወቱን ለማትረፍ ሲል ሶርያዊ ወደሆነው ወደ እናቱ ወንድም ወደ ላባ መስጴጦምያ ወደሚባለው ሥፍራ ሸሸ፡፡ (27፡41-46)

***በእግዚአብሔር መንገድ ሳይሆን በራሳችን ምድራዊ ጥበብና በአሮጌው ሰው ማንነት በረከትን ለማግበስበስ የምንሞክረው አካሔድ ሁሉ የአእምሮና የመንፈስ እረፍት ሊሰጠን ፈጽሞ አይችልም፡፡ ነጻነታችን ይገፈፋል፡፡ እንሸሻለን፡፡ የእኛስ አካሄድ እንዴት ይሆን?***

II. <u>**ያዕቆብ ከላባ ጋር ታገለ፡፡**</u>

ያዕቆብ ከዔሳው ሸሽቶ ወደ ላባ ከሄደ በኋላ ደግሞ ከላባ ጋር ትግል ውስጥ ገብቷል፡፡ በላባ ቤት ውስጥ ያዕቆብ ለልያ 7 ዓመታት፣ ለራሔል 7 ዓመታት፣ ለመንጋዎቹ ደግሞ 6 ዓመታት በጠቅላላ 20 ዓመታት ያህል ተገዝቷል፡፡ በዚህ ሁሉ ብዙ ትግል አሳልፏል፡፡

በመጨረሻ ያዕቆብ ላባ ሳያውቅ፣ እርሱን በማታለል ወደ አባቶቹ ቤት መጓዝ ጀመረ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ በማለት ይናገራል፡- **"ያዕቆብም ቢሆን፣ መኮብለሉን ለሶርያዊው ለላባ ሳይገልጥለት በመቅረቱ <u>አታልሎታል</u>፡፡"** (31፡20)

ላባም ዘመዶቹን ይዞ ያዕቆብን ሊጎዳው በማሰብ ተከታተለው፡፡ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለላባ "በሕልም ተገልጦ ያዕቆብን ክፉም ሆነ ደግ፣ እንዳትናገረው ተጠንቀቅ አለው፡፡" (31፡24)

ላባም ለያዕቆብ በግልጽ <u>"አታለልኸኝ"</u> (31፡26) አለው፡፡ በተጨማሪ <u>"ለምን አታለልኸኝ</u>?" (31፡27) በማለት ጠይቆታል፡፡

ወገኖች ሆይ፡- የእኛስ ሕይወት ምን ይመስል ይሆን? በእግዚአብሔር መለኮታዊ አሰራር የተመረጥንና በክርስቶስ ኢየሱስ የተዋጀን ሰዎች እግዚአብሔር ለእኛ ያዘዘጋጀውን መልካም ነገር በራሳችን መንገድ፣ ብቃት፣ ሃይል፣ ጉልበት፣ ዘዴ፣ እውቀት፣ ብልጣ ብልጥነት፣ ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን በመጨፍለቅ የራሳችን ለማድረግ እተራመድን ይሆን፡፡ በስጋዊ ትግል የምንፈልገውን ማንኛውንም ነገር ለማግኘት ስንል ከሌሎች ሰዎች ጋር በመታገል የምናምን አታላዮች ሆነን እግዚአብሔር እየተመለከተን ይሆን፡፡

እግዚአብሔር ይህንን ማንነት በመለኮታዊ አሰራሩ መለወጥ ይፈልጋል፡፡ በቀድሞ አካሄዳችን ንስሐ በመግባት እግዚአብሔር እንዲለውጠን ራሳችንን እንስጥ!

## III. <u>በመጨረሻም ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር ታገለ፡፡</u>

**ዘፍጥረት 32፡22-32**

ይህ ክፍል ያዕቆብ ከመስጴጦምያ ተመልሶ ቤተሰቦቹን፣ አገልጋዮቹንና መንጋዎቹን ይዞ ሲጓዝ ወደ ተስፋይቱ ምድር ወደ ከነዓን ከመግባቱ በፊት ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት መገናኘቱን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ ሥፍራ እግዚአብሔር የጭኑን ሹልዳ በመንካት እንዲያነክስ ካደረገው በኋላ ያዕቆብን ባረከው፡፡ ይህ ክስተት በያዕቆብ ሕይወትና ታሪክ ውስጥ እጅግ ወሳኝ ለውጥ ያመጣ ክስተት ነው፡፡

ያዕቆብ የያቦቅን ወንዝ ተሻግሮ ወደ ተስፋይቱና ወደ በረከት ምድር ከመግባቱ በፊት ከእግዚአብሔር ጋር መታገል ነበረበት፡፡ <u>ይህ ክፍል የሚያተኩረው በእግዚአብሔርና በያዕቆብ መካከል ስላለው ትግል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ዋነኛው ዓላማው ግን ያዕቆብን ወደ እስራኤል መለወጥ ነው፡፡</u>

ይህ ክፍል እግዚብሔርና ያዕቆብ ያለ ማንም ተመልካችና ረዳት ብቻቸውን ፊት ለፊት የተገናኙበትና የታገሉበት ክፍል ነው፡፡ ይህ ያዕቆብ በዚህ ሥፍራ የታገለው ትግል ከዔሳውና ከላባ ጋር እንዳደረገው ዓይነት ሳይሆን የተለየ ትግል ነው፡፡

<u>ከዚህ በመቀጠል በዚህ ታሪክ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ነጥቦች እንመለከታለን፡፡</u>

1. <u>እግዚአብሔር ሰዎችን ለብቻቸው ሊያገኛቸው ይፈልጋል፣ ሁኔታዎችንም ያመቻችላቸዋል፡፡ ራሳችንን እንስጥ!</u>
    - እግዚአብሔር ያዕቆብን ለብቻው ሊያገኘው ስለፈለገ በግሉ ሊያገኘው የሚችልበትን ልብና ሁኔታ አዘጋጀ፡፡

ያዕቆብና ቤተሰቡ ወደ ያቦቅ ወንዝ ከደረሱ በኋላ ቤተሰቡንና መንጋውን ሁሉ የያቦቅን ወንዝ አሻግሮ ከሸኛቸው በኋላ እርሱ ራሱ ግን ብቻውን ወደኋላ ቀረ፡፡ ያዕቆብ ወደ ተስፋይቱ ምድር ወደ ከነዓን ለመግባት ባሰበበት ጊዜ የእርሱ እድል ፈንታ ያለው በእግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ በሚገባ ሳይገነዘብ አይቀርም፡፡

*"ያዕቆብ ግን ብቻውን እዚያው ቀረ፤ አንድ ሰውም እስኪነጋ ድረስ ሲታገለው አደረ፡፡" (32፡24)*

በዚህ ሥፍራ <u>"አንድ ሰው"</u> የሚለው ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው፡፡ እግዚአብሔር ራሱ በመልዓክ መልክ ከያዕቆብ ጋር ታገለ (ሆሴዕ 12፡3-4)፡፡ ምክንያቱም ያዕቆብ ራሱ በቁጥር 30 ላይ <u>"እግዚአብሔር"</u> በማለት ገልፆታል፡፡

2. <u>ከሰዎች ጋር ታግለን እንዳሸነፍን ቢሰማንም፣ እግዚብሔር ግን የማይሸነፍ ታጋይ መሆኑን እንወቅ፡፡ እርሱ ያሸንፈናል!</u>
    - ከዔሳውና ከላባ ጋር በአታላይነት፣ በራሱ ብርታትና ኃይል የታገለው ያዕቆብ አሁን ግን ሊታለልና ሊሸነፍ ከማይችል አምላክ ጋር በተለየ መንገድ ትግል አካሄደ፡፡

*"ያም ሰው ያዕቆብን ታግሎ ማሸነፍ እንዳቃተው በተረዳ ጊዜ፣ የጭኑን ሹልዳ ነካው፤ በግብ ግቡም የያዕቆብ ጭን ከመጋጠሚያው ላይ ተናጋ፡፡" (32፡25)*

ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር ያዕቆብን ማሸነፍ እንዳቃተው ይሆን የሚናገረው? አይደለም! ለመሆኑ ያዕቆብ ከዔሳውና ከላባ ጋር የታገለው ትግልና አሁን ከእግዚአብሔር ጋር የሚታገለው ትግል አንድ ዓይነት ነውን? አይደለም! ይህ የሚያመለክተው ያዕቆብ ከእግዚብሔር ውጭ ሌላ ዕድል ፈንታ እንደሌለው በመረዳት እግዚአብሔርን ለበረከት የሙጥኝ ብሎ መያዙን የሚያሳይ ነው፡፡

<u>ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለያዕቆብ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ተገልጦ፣ ከእርሱ ጋር በብርቱ እንዲታገል ከመልካምነቱና ከተስፋ ቃሉ የተነሳ ዕድል ቢሰጠውም፤ በማንኛውም ጊዜ፣ በየትኛውም ቦታና በማንኛውም ሁኔታ ያዕቆብን ሊሰባብረው እንደሚችል አሳይቶታል፡፡</u>

ያዕቆብ ከዚህ በፊት በአታላይነቱ፣ በራሱ ጉልበትና ችሎታ ዔሳውንና ላባን ማሸነፍ ቢችልም አሁን ግን ከእግዚአብሔር ጋር ባደረገው ትግል በእግዚአብሔር መለኮታዊ ምት የጭኑ ሹልዳ በመመታቱ መጋጠሚያው ተናጋ፡፡ የማይሸነፍ ታጋይ ስለገጠመው ለእግዚአብሔር እጅ ሰጠ፡፡

ለማንም የማይበገር ሰው፤ በትዕቢት፣ በኩራት፣ በአታላይነት፣ በእኔነት፣ ወዘተ ልቡ የተነፋ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት ሲገናኝ ለእግዚአብሔር ይሸነፋል፣ ይረታል፣ እጅ ይሰጣል፡፡ ያዕቆብ ወደ ከነዓን ከመግባቱ በፊት እግዚአብሔር ከያዕቆብ ጋር በመታገል ሙሉ በሙሉ ራሱን ለእግዚአብሔር እንዲሰጥ አድርጎታል፡፡

ወደ ጌታ በመጠጋት ትዕቢተኛ ልባችን እንዲሸነፍ እንፍቀድ!

3. <u>በእግዚአብሔር የተሸነፉ ሰዎች በረከትን በራሳቸው መንገድ ሳይሆን በእግዚብሔር መንገድ ከራሱ ከእግዚአብሔር ይፈልጋሉ፡፡</u>
    - ምንም እንኳ ያዕቆብ የጭኑ ሹልዳ በመነካቱ የጭኑ መጋጠሚያ ቢናጋም የሚታገለውን ሰው (እግዚአብሔርን) "ካልባረክሽኝ አልለቅህም" በማለት የሙጥኝ ብሎ ያዘው፡፡

*"በዚያን ጊዜ ሰውየው፣ እንግዲህ መንጋቱ ስለሆነ ልቀቀኝና ልሂድ አለው፡፡ ያዕቆብም ካልባረክሽኝ አልለቅህም አለው፡፡" (32፡26)*

በራስ ወዳድነት፣ በማታለልና በጉልበቱ ለራሱ ይታገል የነበረው ያዕቆብ አሁን ግን ለእግዚብሔር እጅ ሰጠ፡፡ ያዕቆብ በረከት የሚገኘው ከእግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ በመጨረሻ ተገነዘበ፡፡ ከዚህ የተነሳ እግዚአብሔርን *"ካልባረክሽኝ አልለቅህም" አለው፡፡* እግዚአብሔር የነካው ሰው ለበረከት ወደ እግዚአብሔር እንጂ ወደ ሌሎች ሰዎች ወይም ሁኔታዎች የመሮጥና የመታገል አማራጭ የለውም፡፡

እኛስ በረከት የምንፈልገው በራሳችን መንገድ በተለያዩ ስጋዊና ጽድቅ የጎደለው አካሄድ ነው ወይስ በእግዚአብሔር መንገድ ከራሱ ከእግዚአብሔር ነው?

4. <u>እግዚአብሔር ስማችንንና ታሪካችንን መለወጥ ይችላል፡፡</u>
    - እግዚአብሔር የያዕቆብን ስም በመለወጥ እስራኤል የሚል ስም ሰጥቶታል፡፡

    *"ሰውየውም፣ ስምህ ማን ነው? አለው፡፡ እርሱም ያዕቆብ ነው አለ፡፡ ሰውየውም፣ ከእግዚአብሔርም ከሰዎችም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና ከእንግዲህ ስምህ እስራኤል እንጂ ያዕቆብ አይባልም አለው፡፡" (32፡27-28)*

በዚህ ክፍል እንደምንመለከተው ያዕቆብ እግዚብሔር ስሙን ሲጠይቀው እውነተኛ ማንነቱን ለመናገር አላፈረም፤ ደግሞም አልፈራም፡፡ <u>እኔ አታላዩ ያዕቆብ ነኝ</u>! በማለት ለእግዚአብሔር መለሰለት፡፡ በእግዚብሔር ፊት ምን የሚደበቅ ነገር አለ?

በዚህ ጥቅስ <u>"ከእግዚአብሔርም … ጋር ታግለህ አሸንፈሃል"</u> የሚለው ቃል ያዕቆብ ከዔሳውና ከላባ ጋር በታገለበት መንገድና ሁኔታ እግዚብሔርን ማሸነፉን ፈጽሞ አያሳይም፡፡

<u>ይህ የእግዚአብሔር ንግግር የሚያሳየው ያዕቆብ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ዓላማ በመስጠቱ ምክንያት ድልን ማግኘቱ ወይም ማሸነፉ ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ስሙን እስራኤል ብሎ በመጥራት ለወጠው።</u>

በነገራችን ላይ፤ ብዙ የብሉይ ኪዳን ስሞች ከሰዎቹ ማንነትና ባህርይ ጋር ይያያዛሉ። "<u>ያዕቆብ</u>" ማለት "<u>ተረከዝ ይይዛል</u>" ወይም "<u>ያታልላል፤ አታላይ</u>" ማለት ነው። "<u>እስራኤል</u>" ማለት "<u>እግዚአብሔር ይታገላል፤ እግዚብሔር ይዋጋል - God strives God fights</u>" ማለት ነው። አታላዩና ራስ ወዳዱ ያዕቆብ አሁን ስሙ ተለወጠ። <u>ይህ "እግዚአብሔር ይታገላል / እግዚአብሔር ይዋጋል" የሚለው ስም ሁለት አንድምታዎች አሉት፦</u>

ሀ) እግዚአብሔር የያዕቆብን አታላይነት፣ ትዕቢት፣ ትምክህተኝነትና ራስ ወዳድነት በመመልከት ያዕቆብን በመታገል ትክክለኛ መስመር ሊያስይዘው መፈለጉ።

ለ) በቀጣይ ዘመኑ እስራኤል ለራሱ እንደማይታገል፤ ይልቁንም እግዚአብሔር ለእስራኤል እንደሚታገልና እንደሚዋጋ ማሳየት።

እግዚአብሔር ያዕቆብ በያዕቆብነቱ ወደ ተስፋይቱ ምድር ወደ ከነዓን እንዲገባ አልፈለገም። ወደ ተስፋይቱ ምድር የሚገባው "<u>ያዕቆብ</u>" ሳይሆን "<u>እስራኤል</u>" ነው። ያዕቆብ በራሱ መንገድ፣ ፈቃድ፣ ብርታትና ኃይል ወደ ከነዓን መግባት አይችልም። በእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር በመሸነፍ ማሸነፍ (ድል ማድረግ) ይቻላል። ለእግዚአብሔር ሕዝብ ድል የሚገኘው በአሕዛብ መንገድ፣ በጦርና በሰይፍ ሳይሆን በእግዚአብሔር ኃይልና በመለኮታዊ ባርኮት ሙላት ነው። በየትኛውም ዘመን ቢሆን የሰው ብቃት ከእግዚአብሔር አሰራር ጋር አይሄድም። ድል የሚገኘው በእምነትና በእግዚአብሔር ላይ በመደገፍ ብቻ ነው።

5. <u>ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት ስንገናኝ ስማችንና ታሪካችን ብቻ ሳይሆን ሁለንተናችን (ባህርያችን) ድኖና ተፈውሶ ይቀራል።</u>
   - ያዕቆብ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት በማየቱ ምክንያት ሰውነቱ ድና ቀረች (ሁለንተናው ተለወጠ፣ ተፈወሰ)።

*"ስለዚህ ያዕቆብ፣ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ፣ ሰውነቴም ድና ቀረች ሲል የዚያን ቦታ ስም ጵኒኤል ብሎ ጠራው።" (32:30)*

"<u>ጵኒኤል</u>" ማለት "<u>የእግዚአብሔር ፊት</u>" ማለት ነው። "<u>እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ</u>" (32:30) የሚለው ሐረግ "<u>እግዚአብሔርን ያየው አንድስ ስንኳ የለም</u>" (ዮሐ 1:18) ከሚለው ሃሳብ ጋር አይጋጭም። በዚህ ክፍል "እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ" የሚለው አባባል ዘይቤያዊ ንግግር ሲሆን "<u>ፍጹም በሆነ ቅርርብ፣ ግልጽነትና ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘትን</u>" የሚያሳይ ነው። እግዚአብሔርን በመለኮታዊ ባህርዩ ማየት ሳይሆን፣ ራሱን በገለጠበት መልክ ማየትን ብቻ የሚያሳይ ነው (<u>ለምሳሌ</u>፦ ለያዕቆብ በሰው (በመልዓክ) አምሳል ተገለጠለት)። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ያዩ ሰዎች ሁለንተናቸው ተፈውሶና ተለውጦ ይቀራሉ፣ ይድናሉ። ይህ ደግሞ ውስጣዊ ባህርይን ጭምር በዋነኛነት የሚያመለክት ነው። በስጋ ስንመለከት ያዕቆብ የጭኑ ሹልዳ በመለኮታዊ ምት በመመታቱ ታፋው ተናግቷል። ነገር ግን ባህርዩ ሙሉ በሙሉ ተለውጧል። አታላዩና በራሱ የሚደገፈው ያዕቆብ አሁን ግን ሙሉ በሙሉ ራሱን ለእግዚአብሔር በመስጠት ዘላቂ ፈውስና እረፍት አግኝቷል። እግዚብሔር ሹልዳውን

በመለኮታዊ ምት ሲነካው ያዕቆብ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ወዲህና ወዲያ ሲባዝን ያላገኘውን እረፍትና እርካታ አሁን አገኘ፡፡

6. <u>በእግዚአብሔር የተነኩ ሰዎች በቀድሞ የእኔነት፣ የትዕቢትና የራስ ወዳድነት ማንነታቸው አይገኙም፡፡</u>
   - እግዚአብሔር በመለኮታዊ ሐይሉ የልባቸውን ሹልዳ የነካቸው ሰዎች ወደ ቀደመው አሮጌው የእኔነትና የራስ ወዳድነት ማንነታቸው መመለስ አይሆንላቸውም፡፡

*"ጵኒኤልንም እንዳለፈ ፀሐይ ወጣችበት፤ እርሱም በጭኑ ምክንያት ያነክስ ነበር፡፡" (32፡31)*

አሁን የያዕቆብ ትዕቢት ተንፍሷል፣ ትምክህቱ ወድቋል፣ እኔነቱ ከስሟል፣ ራስ ወዳድነቱ ሟሽሿል፣ ሥጋዊ መሳርያዎቹ ሽባ ሆነው ከጥቅም ውጭ ሆነዋል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር በነበረው ትግል እነዚህ ፈጽሞ የሚያዋጡ ስላልነበሩ ለእግዚአብሔር እጅ በመስጠት በእግዚአብሔር መንገድ፣ በእግዚአብሔር ጉልበትና በእግዚአብሔር ሐይል ለመራመድ ወስኗል፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ የያዕቆብ ብቃት ከእግዚአብሔር እንጂ ከራሱ አይደለም፡፡

ያዕቆብ በተፈጥሮ ጉልበቱና ማንነቱ መታገል አቁሞ፣ አሁን በእምነት በእግዚአብሔር ላይ ራሱን በመጣል የእምነት ተጋድሎና ትግል ጀመረ፡፡

በቁጥር 31 ላይ <u>"ፀሐይ ወጣችበት"</u> የሚለው ሐረግ ያለፈው የያዕቆብ የጨለማና የምስቅልቅል ሕይወት አልፎ በእስራኤልነቱ የሚታወቅበት አዲስ ዘመን መምጣቱን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ አዲስ ዘመን የሚታወቀው ግን <u>"ያነክስ ነበር"</u> እንደሚለው በማነከሱ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ያዕቆብ በእርሱ ላይ እንዲደገፍ ለማድረግ ያዕቆብ የሚያስታውሰው አሻራ በሥጋው ላይ አስቀምጧል፡፡ ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱሳችን እንዲህ በማለት የሚናገረው፡-

*"ከዚህም የተነሳ የእስራኤል ልጆች እስከ ዛሬ ድረስ ሹልዳን ከጭኑ ጋር የሚያገናኘውን ሥጋ አይበሉም፤ ምክንያቱም በጭኑ መጋጠሚያ ላይ ያለው የያዕቆብ ሹልዳ ተነክቶ ነበር፡፡" (32፡32)*

ይህ ሹልዳን ከጭኑ ጋር የሚያገናኘው ሥጋ ምናልባትም የታፋ ጡንቻ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ይህ ሐረግ ወይም አባባል በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በየትኛውም ቦታ በቀጥታ ተጠቅሶ አናገኘውም፡፡ ይሁን እንጂ ከጊዜ በኋላ በተጻፉ የዕብራውያን መጻሕፍት ውስጥ የታፋን ማለትም የወርች ሹልዳን ሥጋ መብላት የሚከለክል ወይም የሚያወግዝ ሕግ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡[1]

ከላይ እንደተመለከትነው ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገውን ልዩና አስደናቂ የሆነ ትግል በማይረሳና ለዘላለም በሚያስታውስ ሁኔታ ያዕቆብ በሰውነቱ ወይም በአካሉ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ይዞት ይዞራል፡፡ የእርሱ ዘር የሆኑት፣ እግዚአብሔር ሕዝቤ ብሎ የጠራቸው ወገኖች ወይም እስራኤል ደግሞ የሚበላና የማይበላ ምግብን በሚለየው ሥርዓቷ ውስጥ ጠብቀውት ይኖራሉ፡፡[2]

እግዚአብሔር በመለኮታዊ ማንነቱ ፊት ለፊት ያገኛቸው ሰዎች የራሱን መለኮታዊ ምት በእነርሱ ላይ በማሳረፍ መለኮታዊ አሻራ በምልክትነት በውስጣዊ ማንነታቸው ላይ

[1] መጽሐፍ ቅዱስ፤ አዲሱ መደበኛ ትርጉም፣ ከማጥኛ ጽሑፍ ጋር፣ ገጽ 55፡፡
[2] መጽሐፍ ቅዱስ፤ አዲሱ መደበኛ ትርጉም፣ ከማጥኛ ጽሑፍ ጋር፣ ገጽ 55፡፡

ስለሚያስቀምጥ የተዋረደ መንፈስና ትሁት ልብ ይኖራቸዋል፡፡ ወደ ቀደመው አሮጌው ማንነታቸው አይመለሱም፡፡
እግዚአብሔር ውስጣዊ ማንነታችንን በመንካት ትዕቢታችንንና ራስ ወዳድነታችንን ሲያስጥለን በፈሪሃ እግዚአብሔር እንሞላን፡፡ በራሳችን እውቀት፣ ጉልበት፣ ሃይል፣ ችሎታ፣ ወዘተ በትዕቢተኝነትና በትምክህተኝነት መመላለስ እናቆማለን፡፡ ራሳችንን በእግዚአብሔር ላይ በፍጹምነት በመጣል እንደ ልጆች በእግዚአብሔር ላይ በትህትና የተደጋፊነትን ሕይወት እንኖራለን፣ እንለማመዳለን፡፡

ስለዚህ ያዕቆብ ለመለወጥ ራሱን እንደሰጠ ሁሉ እኛም ራሳችንን ለእግዚብሔር ለመስጠት እንፍቀድ! እግዚአብሔር የያዕቆብን የጭኑን ሹልዳ በመንካት እንደለወጠው ሁሉ የእኛንም የልብ ሹልዳ በመለኮታዊ ምት በመንካት ይለውጠናል፡፡ እግዚአብሔር የልባችንን ሹልዳ በመንካት ትእቢታችንን ያስተንፍሰው! ያኔ እንደ ሌላ ሰው ሆነን እንለወጣለን! ያውም እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበትና የሚያርፍበት ሰው!